Bundesamt für Migration und Flüchtlinge

# የመቀላቀል ትምህርትን የሚመለከት መረጃ ጽሑፍ

ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ ጀርመን ውስጥ ለሚኖሩ የውጭ ኣገር ዜጎች፣ የአውሮጳ ሕብረት ዜጎች፣ የኤውሮጳ የቁጠባ ማሕበር ኣባል ኣገሮች ዜጎች እንደዚሁም በቂ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው የጀርመን ዜጎች።

የተከበራችሁ ኗሪዎች፣

ጀርመን ውስጥ ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ የሚኖሩ የውጭ ኣገር ዜጋ ከሆኑ ወይም የኤውሮጳ ሕብረት ዜጋ ከሆኑ ወይም የኤውሮጳ የቁጠባ ማሕበር ኣባል ኣገሮች ዜጋ ከሆኑ ወይም እርስዎ የጀርመን ዜጋ ሆነው በቂ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ የሌለዎት ከሆኑ፣ የመቀላቀል ትምህርት ለመሳተፍ እንዲፈቀድልዎ ለፌደራላዊ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጽሕፈት ቤት ማመልከት ይችላሉ።

ትምህርት ቤት በመኅብኘት ላይ ያሉ ልጆች፣ ወጣቶችና ላቅመ ኣዳም ለደረሱ ወጣቶች፣ እዚህ የመቀላቀል ትምህርት መሳተፍ ኣይችሉም።

<u>የመቀላቀል ትምህርት ምንድን ነው?</u>

የመቀላቀል ትምህርት በመሰረቱ 600 የትምህርት ሰዓታት ያለው የቋንቋ ትምህርትና 100 የትምህርት ሰዓታት ያለው የማስተዋወቂያ ትምህርትን ያካትታል። የቋንቋ ትምህርቱ እያንዳንዱ 100 የትምህርት ሰዓታት የያዙ ክፍሎች ኣሉት። የመጀመሪያዎቹ 300 የትምህርት ሰዓታት መሰረታዊ የቋንቋ ትምህርት ተብለው ሲጠሩ፣ የሚቀጥሉት 300 የትምህርት ሰዓታት ደግሞ የቋንቋ ማሻሻያ ትምህርት ይባላሉ።

በቋንቋ ትምህርቱ የሚማሩት ለዕለት ከዕለት ለመናገርና ለመጻፍ የሚያስፈልግዎትን ቃላቶች ይማራሉ። ከጽሕፈት ቤቶች ጋር ለሚደረጉት ግኑኝነቶች፣ ከጎረቤቶችና ከስራ ባልደረባዎች ጋር መወያየት፣ ደብዳቤዎች መጻፍና ፎርሙላዎች መሙላትን በዚህ ትምህርት ይጠቃለላሉ።

የማስተዋወቂያው ትምህርት ጀርመን ውስጥ ስላለው ሕይወት መረጃ ይሰጥዎታል እንደዚሁም ስለ ሕጋዊ ስርዓት፣ ባህልና የቅርብ ጊዜ ታሪክ እውቀት ያቀስምዎታል።

በተጨማሪም ልዩ የሆነ የመቀላቀል ትምህርት ለምሳሌ ለሴቶች፣ ለወላጆች፣ ወጣቶች እንደዚሁም በደንብ መጻፍና ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ኣለ። እነዚህ ትምህርቶች 1000 የትምህርት ሰዓታት ይወስዳሉ። በልዩ ፍጥነት መማር የሚችሉ ከሆነ፣ ፈጣኑን ትምህርት መማር ይችላሉ። ይህ ትምህርት 430 የትምህርት ሰዓታት ነው የሚወስደው።

የትኛው ትምህርት ለርስዎ ትክክለኛ እንደሆነና በየትኛው ክፍል መጀመር እንዳለብዎት፣ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ትምህርት ሰጪው ተቋም በኣንድ ፈተና ያረጋግጣል።

<u>በመጨረሻው ፈተና መሳተፍ</u>

የመጨረሻው ፈተና የቋንቋ ፈተናና የማስተዋወቂያ ፈተናን ያካትታል። በቋንቋው ፈተና በቂ የሆነ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ እንዳለዎት ካሳዩና የማስተዋወቂያውን ትምህርት ፈተና ካለፉ፣ የመቀላቀል ትምህርቱን በተሳካ ሁኔታ ኣጠናቀዋል ተብለው „የመቀላቀል ትምህርት ሰርቲፊኬት“ ይቀበላሉ።

በተሳካ ሁነታ ካልጨረሱ፣ ያመጡትን ዉጤቶች የሚገልጽ ብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጥዎታል።

በመጨረሻው ፈተና መሳተፍ ከክፍያ ነጻ ነው።

<u>በመቀላቀል ትምህርት መሳተፍ የሚገኙ ጥቅሞች</u>

KNr. 630.009k Amharisch BAMF 11/2017

የኤውሮጳ ሕብረት አባላት ካልሆኑ አገሮች የመጡ የውጭ አገር ዜጎች፣ በጀርመን ቋሚ የሆነ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ከፈለጉ፣ አንዳንድ ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ነገሮች አሉ። ማሟላት ካለባቸው ነገሮች ውስጥ በቂ የሆነ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ እንደዚሁም ስለ ሕጋዊ እና ስለ ማሕበረሰባዊ ስርዓትና ጀርመን ውስጥ ስላለው የሕይወት ሁኔታ መሰረታዊ የሆነ እውቀት ሊኖርዎት እንደሚገባ ይገኙበታል። የመቀላቀያውን ትምህርት በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ፣ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተዋል። ከዚህ በተረፈም ምናልባት አስቀድመው የአገር ዜግነት ማግኘት ይችላሉ።

ከዚህ አልፎም በዚህ በመቀላቀል ትምህርት የሚቀስሟቸው የጀርመንኛ ቋንቋ እውቀቶች በጀርመን አገር ውስጥ የሚኖርዎትን የዕለታዊ ኑሮዎን ሊያቀልልዎትና ስራ የማግኘት ዕድልዎን ከፍ ሊያደርግ ይችላል።

## ከፌደራሉ ጽሕፈት ቤት ለመቀላቀል ትምህርት ፈቃድ ማግኘትና በትምህርት ሰጪው ተቋም መመዝገብ

እባክዎን የማስፈቀጃ ማመልከቻውን ሙሉ በሙሉ በደንብ ሊነበብ እንደሚችል አድርገው ይምሉት። ማመልከቻውን ለመሙላት እንዲረዳዎት፣ ባቅራቢያዎ የሚገኘውን የትምህርት ሰጪ ተቋም መጠየቅ ይችላሉ። ማመልከቻውን እርስዎ ለሚኖሩበት አገር ሓላፊነት ወዳለው የፌደራል ጽሕፈት ቤቱ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ይላኩት።

በአንድ የመቀላቀል ትምህርት ለመሳተፍ ከተፈቀደልዎት፣ ከፌደራሉ ጽሕፈት ቤት አንድ የጽሑፍ ማረጋገጫ (የፈቃድ ማረጋገጫ ወረቀት) ይላክልዎታል። ከዚሁ ጋርም በሚኖሩበት አከባቢ የሚገኙ የመቀላቀል ትምህርት የሚሰጡ ተቋሞች ዝርዝር የያዘ ሊስታ ያገኛሉ።

የሚላክልዎት የመቀላቀል ትምህርት ፈቃዱ ለአንድ ዓመት ያገለግላል። በማረጋገጫው በታች በኩል „የመሳተፍ ፈቃድ ወረቀት የሚያገለግለው እስከ…“ አንድ ዕለት ሰፍሯል፣ እዚህ እስከተጠቀሰው ዕለት ድረስ በአንድ የመቀላቀል ትምህርት በሚሰጥ ተቋም መመዝገብ ይችላሉ። እባክዎን በአንድ ምናልባትም በተጠቀሰልዎት ቦታ ለአንድ የመቀላቀል ትምህርት ይመዝገቡ እንደዚሁም የፈቃድ ማረጋገጫ ወረቀት እዛ ያቅርቡት። ለርስዎ አንድ የተወሰነ ቦታ ያልተጠቀሰልዎት ከሆነ፣ በተቻልዎት መጠን ፈጠን ብለው በአንድ እርስዎ በመረጡት ትምህርት ሰጪ ተቋም ይመዝገቡ።

ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የርስዎን በጊዜ ትምህርት መሳተፍዎን ለማረጋገጥ ብሎ ወደ አንድ ትምህርት ሰጪ ተቋም ሊልክዎት ይችላል።

ትምህርት ሰጪው ተቋም የሚቀጥለው ትምህርት መቼ እንደሚጀምር እርስዎን ማሳወቅ አለበት። ትምህርቱ የሚጀምረው ከተመዘገቡ በኋላ ስድስት ሳምንታት ማሳለፍ የለበትም። በዚህ ወቅት የመቀላቀል ትምህርት የማይጀመር ከሆነ፣ የትምህርት ተቋሙ እርስዎን ማሳወቅ አለበት። የትምህርት ተቋም የሚቀይሩ ከሆነ፣ አስቀድመው የነበሩበት የትምህርት ተቋም የፈቃድ ማረጋገጫ ወረቀቱን ለርስዎ መመለስ አለበት።

በርስዎ ሓላፊነት ምክንያት ከተመዘገቡ በኋላ ቢዘገይ አንድ ዓመት ሳያልፍ የመቀላቀል ትምህርቱን ያልጀመሩ ከሆነ ወይም የትምህርት ተሳታፊነቱን ከአንድ ዓመት በላይ ያቋረጡ ከሆነ፣ የመሳተፍ ፍቃዱ እንደሚሰረዝ እባክዎን ያስተውሉ።

## ስርዓቱን ጠብቆ ትምህርት መሳተፍ

የመቀላቀል ትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲችሉ፣ ስርዓቱን ጠብቀው በትምህርቱ መሳተፍ አለብዎት። ይህ ማለት፣ በትምህርት ገበታውን ሳያቋርጡ መገኘት አለብዎት እንደዚሁም የመጨረሻውን ፈተና መውሰድ አለብዎት። በሚቀጥለው ጊዜ የቋንቋ ትምህርት ሰዓታትን መድገም ከፈለጉ፣ ስርዓቱን ጠብቀው በትምህርቱ መሳተፍ ለርስዎ አስፈላጊ ነው። የትምህርት ሰጪው ተቋም፣ እርስዎ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ስርዓቱን ጠብቀው እንደሚሳተፉ በጽሑፍ ማረጋገጫ ሊሰጥዎት ይችላል።

የትምህርት ተቋሙን መቀየር የሚቻለው በመሰረቱ አንድ የትምህርት ክፍል ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ ነው የሚቻለው። መቀየር የሚቻለው ልዩ የሆነ ሁኔታ ሲኖር ነው፣ በተለይም ቤት የቀየሩ እንደሆን፣ ከግማሽ ቀን ወደ ሙሉ ቀን ትምህርት የቀየሩ እንደሆነ፣ ልጅን ለመንከባከብ እንዲመች ወይም አንድ የትምህርት ክፍል ከጨረሱ በኋላ የሙያ ትምህርት ወይ ደግሞ ስራ የሚጀምሩ ከሆነ ነው የሚቻለው።

## ለመቀላቀል ትምህርት የሚከፈል ክፍያ

ትምህርት ለሚሰጠው ተቋም ለያንዳንዱ የትምህርት ሰዓት 1,95 ኦይሮ መክፈል ኣለብዎት። ይህ ክፍያ እያንዳንዱ 100 የትምህርት ሰዓታት ያለው የትምህርት ክፍል ከመጀመሩ በፊት እንደዚሁም የማስተዋወቂያ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት መከፈል ኣለበት። ትምህርት ሲሰጥ ሳይገኙ የቀሩ ከሆነ፣ ለነዚህ ላመለጥዎት ሰዓታት የከፈሉት ክፍያ ሊመለስልዎት ኣይችልም። እርስዎ ራስዎ የሚያገኙት ገቢ የሌለዎት ከሆነ፣ የርስዎን መተዳደርያ ለመሸፈን ግዴታ ያለበት ግለሰብ፣ እነዚህን ክፍያዎች መክፈል ኣለበት።

በስራ ኣጥ ገንዘብ II ወይ ደግሞ በማሕበራዊ የቀለብ ማረጋገጫ (Sozialhilfe) የሚኖሩ ከሆነ ወይ ደግሞ ዝቅተኛ የሆነ ገቢ ስላለዎት ለመክፈል የማይችሉ ከሆነ፣ ክፍያ ከመክፈል ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ። ከክፍያ ነጻ ለመሆን ከፈለጉ፣ ለርስዎ ሓላፊነት ላለው፣ ለፌደራል ጽሕፈት ቤቱ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ኣለብዎት (የኣድራሻ ዝርዝሩን ይመልከቱ)።

የገንዘብ እጥረት እንዳለብዎት የሚያረጋግጡን ሰነዶች ኣያይዘው ያቅርቡ (ይህንን የሚመለከቱ የምስክር ወረቀቶች ቅጂ፣ ለምሳሌ የስራ ኣጥነት II ክፍያ፣ የማሕበራዊ እርዳታ፣ የመኖሪያ ቤት ገንዘብ፣ ለተማሪ የሚሰጥ እርዳታና ለልጆች ተጨማሪ ክፍያ መግለጫ፣ ጥገኝነት ላመለከተ እርዳታ በሚያሰጥ ሕግ መሰረት የተደጎሚነት ማረጋገጫ፣ ከመዋእለ ሕጻናት ክፍያ ነጻ መሆን ማረጋገጫ፣ ከሚዲያ ክፍያ ነጻ መሆን የሚያረጋግጥ፣ የክልልዎ የመጓጓዣ ማሕበራዊ ቲኬት፣ በማሕበራዊ መጽሓፍ ሕግ III መሰረት የልጆችና የወጣቶች እርዳታ ፈቃድ ወ.ዘ.ተ.)። ይሄንን ማመልከቻ በተቻልዎት መጠን ትምህርት መሳተፍ ከመጀመርዎ በፊት ያቅርቡ። ማመልከቻውን መማር ከጀመሩ በኋላ ካቀረቡ፣ በመሰረቱ ከክፍያ ነጻ የሚሆኑት ወደ ኋላ ተመልሶ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ኣይሆንም።

## የልጆች እንክብካቤ

በዚህ የመቀላቀል ትምህርት ለመሳተፍ ልጆች የሚንከባከብ የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ ትምህርት ለሚሰጠው ተቋም ይሄንን ይንገሩ። ተቋሙ ስላሉት የእንክብካቤ ኣማራጮች መረጃ ይሰጥዎታል።

## ክፍያን ማስመለስ

ከ 08.12.2007 በኋላ የመጨረሻውን ፈተና ስኬታማ በሆነ ውጤት ያጠናቀቁ ከሆነ፣ የፌደራላዊ ጽሕፈት ቤቱ ከከፈሉት ክፍያ 50% መልሶ ሊከፍልዎት ይችላል። ይህን ክፍያ ሊያስመልሱት የሚችሉ፣ የመጀመሪያው የመሳተፍ ፈቃድ ከተሰጠዎት በኋላ ሁለት ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ የመጨረሻውን ፈተና የተፈተኑ እንደሆነ ብቻ ነው። ክፍያውን ለማስመለስ በሚመለከተው ለፌደራል ጽሕፈት ቤቱ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ኣለብዎት።

## የመጓጓዣ ክፍያዎች

በፌደራሉ ጽሕፈት ቤት በኩል ከትምህርት ክፍያው ነጻ የሆኑ ከሆነ፣ የመቀላቀል ትምህርት ለመከታተል የመጓጓዣ ክፍያ ድጎማ ሊያገኙ ይችላሉ። ድጎማው የሚሰጠው ለያንዳንዱ የትምህርት ቀን በሚል ኣጠቃላይ መልክ ነው። ለዚሁ ቅድመ ሁኔታው ግን ትምህርት የሚሰጥበት ቦታ ከመኖሪያ ቤትዎ ቢያንስ የ 3 ኪሎሜትር ርቀት ያለው ከሆነ ነው። የመጓጓዣ ክፍያ ድጎማ ለማግኘት በሚመለከተው ለፌደራል ጽሕፈት ቤቱ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ኣለብዎት።

## የቋንቋ ማሻሻያ ትምህርቱን መድገም

በቋንቋ ፈተናው በቂ የሆነ የጀርመንኛ ችሎታ ማሳየት ካልቻሉ፣ ኣንድ ጊዜ እስከ 300 የትምህርት ሰዓታት የቋንቋ ትምህርት መድገምና በድጋሚ ደግሞ ከክፍያ ነጻ ሆነው በቋንቋ ፈተናው መሳተፍ ይችላሉ። ለዚህ ቅድመ ሁኔታው ግን፣ መደበኛውን ትምህርት ሳይቀሩ የተከታተሉ እንደሆነ ነው።

በኣንድ የመሰረተ ትምህርት የተማሩ ከሆነ፣ በቋንቋ ፈተናው መሳተፍ ኣስፈላጊ ኣይደለም።

የመድገም የትምህርት ሰዓታት ለመሳተፍ በሚመለከተው ለፌደራል ጽሕፈት ቤቱ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ኣለብዎት።

ሌላ ማወቅ ያለብዎት ምን አለ

እዚህ የመረጃ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ የማመልከቻ ፎርሙላዎችን ትምህርት ከሚሰጠው ተቋም፣ እርስዎን ከሚመለከት የውጭ አገር ዜጎች ጽሕፈት ቤት ወይ ደግሞ ከሚመለከተው የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ያገኛሉ። ከዚህ በተረፈም እነዚሁን ፎርሙላዎች በኢንተርኔት ገጽ www.bamf.de ያገኛሉ። የመረጃ ጽሑፉ በመቀላቀያ ትምህርቱ ለመሳተፍ የሚያስችሉ ለርስዎ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች አሉት። ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ከትምህርት ሰጪው ተቋም ያገኛሉ።

ከዚህ ውጭም የስደተኞች ማማከሪያ ጽሕፈት ቤትና የወጣት ስደተኞች አገልግሎት የሚያቀርቡትን እባክዎ ያስተውሉት። እነዚህ ተቋማት ማመልከቻዎችን በሚመለከት ይረዳሉ፣ ጥያቄዎን ይመልሳሉ እንደዚሁም ችግርዎን ለመፍታት ይጥራሉ እርስዎን የሚስማማ የመቀላቀል ትምህርትም ሊፈልጉ ይችላሉ። የስደተኞች ማማከሪያ ጽሕፈት ቤትና የወጣት ስደተኞች አገልግሎት መስጫ ባካባቢዎ የት እንደሚገኝ ለማወቅ ከፈለጉ፣ ከውጭ አገር ዜጎች ጽሕፈት ቤት፣ ከሚመለከተው ለፌደራል ጽሕፈት ቤቱ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይ ደግሞ ከኢንተርኔት ገጽ www.bamf.de ማግኘት ይችላሉ።

አንድ የመቀላቀል ትምህርትን በሚከታተሉበት ወቅት ሕጋዊ የሆነ የአደጋ ኢንሹራንስ እንደሌለዎት እባክዎን ያስተውሉ።